ውድ አንባቢ፥

የመሲሑን መምጣት የሚገልጥ ትንቢት ከእግዚአብሔር ዘንድ ለነቢዩ ዳንኤል ተሰጠው። ይህም የሆነው ኢየሱስ ከመወለዱ ከአምስት መቶ ዓመታት በፊት ነው። ትንቢተ ዳንኤል፥ በቶራኽ (በብሉይ ኪዳን) ውስጥ ተዘግቦ ይገኛል። የትንቢቱ አፈጻጸም አስደናቂና የብዙዎችን ትኩረት የሳበ ሲሆን፥ ይህ ትንቢት በቶራኽ (በብሉይ ኪዳን)ና በኢንጅል (አዲስ ኪዳን) እንዲሁም በዓለም ታሪክ ውስጥ ሁሉ ይገኛል።

## ትንቢተ ዳንኤል

ከብሉይ ኪዳን፥ ከትንቢተ ዳንኤል የተወሰደ ጥቅስ እንዲህ ይነበባል፡- ዳንኤል 9፡25-26

> «ስለዚህ እወቅ አስተውልም፤ ኢየሩሳሌምን መጠገንና መሥራት ትእዛዙ ከሚወጣበት ጀምሮ። እስከ አለቃው እስከ መሲሕ ድረስ ሰባት ሱባዔና ስድሳ ሁለት ሱባዔ ይሆናል፤ እርስዋም በጭንቀት ዘመን ከጎዳናና ከቅጥር ጋር ትሠራለች። ከስድሳ ሁለት ጊዜ ሰባትም በኋላ መሲሕ ይገደላል፥ በእርሱም ዘንድ ምንም የለም፤የሚመጣውም አለቃ ሕዝብ ከተማይቱንና መቅደሱን ያጠፉሉ፤ ፍጻሜውም በጐርፍ ይሆናል፥ እስከ መጨረሻም ድረስ ጦርነት ይሆናል፤ ጥፋትም ተቀጥሮአል»

በቶራኽ መሠረት ከላይ የሠፈረው ትንቢት ከእግዚአብሔር ዘንድ ለዳንኤል የተሰጠው በአሕሻዊሮስ ልጅ በዳርዮስ የመጀመሪያ የንግሥና ዓመት ነበር (ዳንኤል 9፡1)። ዳርዮስ ከ539 ዓመተ ዓለም እስከ 525 ዓመተ ዓለም ድረስ የፋርስ ንጉሥ እንደነበር ታሪክ ይዘግባል።

«የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶቹ የተወሰዱት ከአሮጌው ትርጉም ነው።»

«የቁርአን ጥቅሶች የተወሰዱት በ38ኛው ዘመን ከታተመው የቁርአን መጽሐፍ ነው።»

## 1. የትንቢተ ዳንኤል አፈጻጸም

«...<u>ኢየሩሳሌምን መጠገንና መሥራት ትእዛዙ ከሚወጣበት ጀምሮ</u>...»

ኢየሩሳሌምን ለመመለስና ለመገንባት የተሰጠው ትእዛዝ የወጣው ከንጉሥ አርጤክስስ ነበር። ይህም ከዳንኤል ትንቢት ከዘጠና ዓመታት በኋላ ነበር። ትእዛዙ በብሉይ ኪዳን ውስጥ በመጽሐፈ ነህምያ 2፡1-9 ሰፍሮ እናገኘዋለን። የተጻፈውን ከመጽሐፉ ስናነብ ንጉሡ ኢየሩሳሌም መልሳ ትገነባ ዘንድ ነህምያን ወደ ከተማይቱ ተመልሶ እንዲሄድ አድርጓል። ይህም በአርጤክስስ በሃያኛው የንግሥ ዘመን እንደነበር በነህምያ 2፡1 ከሰፈረው ለመረዳት እንችላለን። የፋርሱ አርጤክስስ የንግሥ ዘመን ከ 464-423 ዓመተ ዓለም ድረስ ነበር። ንጉሥ አርጤክስስ ኢየሩሳሌም ትገነባ ዘንድ የሰጠው ትእዛዝ በ445 ዓመተ ዓለም ነበር።

«እስከ አለቃው» እስከ መሲሕ ድረስ ሰባት ሱባዔና ስድሳ ሁለት ሱባዔ ይሆናል፤ እርስዋም በጭንቀት ዘመን ከጎዳናና ከቅጥር ጋር ትሠራለች።

## 2. የትንቢተ ዳንኤል አፈጻጸም

«...<u>እስከ አለቃው እስከ መሲሕ ሰባት ሱባዔና ስድሳ ሁለት ሱባዔ ይሆናል</u>፤»

በዕብራውያን ሱባዔ የሚለው ቃል ሰባት የሚል ትርጉም ይኖረዋል። ስለዚህ የቃሉ ይዘት የሚያመለክተው ሰባት ዓመታትን የሚያካትት ጊዜን ነው። በዚሁ አኳያ የሰባት ሱባዔና ስድሳ ሁለት ሱባዔ የሚኖረው ፍቺ ሰባት ዓመት ሰባት ጊዜ ስድሳ ሁለት ሰባት ዓመትን የያዘ የጊዜ ስሌቱ ወደ 483 የአይሁድ ዓመታት ወይም ከእኛው 476 ዓመታት፥ ይኸውም ኢየሱስ በውርንጭላ ላይ ተቀምጦ በሕዝብ ፊትና በአደባባይ መሲሕ መሆኑን በይፋ ያስተዋወቀበት ጊዜ ላይ ያደርሰናል። ስለዚህ ሁኔታ በኢንጅል በዮሐንስ 12፡12-16 ከተጻፈው እናነባለን። በተጨማሪ ኢንጅል በሉቃስ 3፡1-22 ጴንጤናዊው ጲላጦስ የአይሁድ ገዥ በነበረ ጊዜ ሁለቱም ማለት መጥምቁ ዮሐንስና ኢየሱስ የሰብከት አገልግሎት ይሰጡ ነበር። የሮማውያን ታሪክም ጴንጤናዊው ጲላጦስ ከ26-36 ዓመተ ምሕረት እንደ አውሮፓ አቆጣጠር የአይሁድ ገዥ እንደነበር አስፍሯል።

ከስድሳ ሁለት ጊዜ ሰባትም በኋላ መሢሕ ይገደላል፥ በእርሱም ዘንድ ምንም የለም፤

## 3. የትንቢተ ዳንኤል አፈጻጸም

«...ከስድሳ ሁለት ሳምንታት በኋላ መሢሕ ይገደላል፥»

ስለሆነም፥ በቶራኽ ውስጥ ከስድሳ ሁለት ሰባት ዓመት ጊዜ በኋላ ማለት ሰባት ሰባት ዓመት ተከትሎ ባለው ጊዜ ውስጥ መሢሑ እንደሚገደል ነቢዩ ዳንኤል ተንብዮ ነበር። ኢየሱስም ራሱ በምድር ላይ ባደረጋቸው ሦስት የተለያዩ የስብከት ጊዜያት ላይ ስለመገደሉ የተነገረውን ትንቢት በማረጋገጥ ተናግርአል።

ሀ) ኢየሱስ ከመሞቱ ከዘጠኝ ወራት በፊት የተናገረውን ኢንጅል እንዳሰፈረው:-

«የሰው ልጅ ብዙ መከራ ሊቀበል፥ ከሽማግሌዎችም ከካህናት አለቆችም ከጻፎችም ሊጣል፥ ሊገደልም ከሦስት ቀንም በኋላ ሊነሣ እንዲገባው ያስተምራቸው ጀመር» (ማርቆስ 8:31)።

ለ) በመቀጠልም ኢየሱስ ከመሞቱ ከስድስት ወር በፊት ለሐዋርያቱ እንዲህ አላቸው:-

«የሰው ልጅ በሰዎች እጅ አልፎ ይሰጣል፥ ይገድሉትማል፥ ተገድሎም በሦስተኛው ቀን ይነሣል ይላቸው ነበር» (ማርቆስ 9:31)።

ሐ) ሐዋርያቱ የነገራቸውን ያስተውሉ ዘንድ እንደገና ሊገደል ጥቂት ቀናት ብቻ ሲቀረው እንዲህ ሲል አስታወሳቸው:-

«...እነሆ፥ ወደ ኢየሩሳሌም እንወጣለን፥ ስለ ሰው ልጅም በነቢያት የተጻፈው ሁሉ ይፈጸማል። ለአሕዛብ አሳልፈው ይሰጡታልና፥ ይዘብቁበትማል ያንገላቱትማል ይተፉበትማል፤ ከገረፉትም በኋላ ይገድሉታል፥ በሦስተኛውም ቀን ይነሣል» (ሉቃስ 18:31-33)።



ከዚሁ በኋላ ኢየሱስ ስለ ሞቱ እንዲህ በሚል ቃል ገልጾታል:-

«... የሰው ልጅም ሊያገለግልና ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም» (ማር. 10:45)።

ኢንጅል ኢየሱስ ከሌሎች ሁለት ሰዎች ጋር መሰቀሉን ይናገራል። ክቡር የሆነችዋ ዕለተ ሰንበት ከመድረስዋ በፊት፥ የሦስቱም ተሰቃይ ሰዎች ሕይወት ባፋጣኝ ታልፍ ዘንድና ሬሳቸውም ገና በዋዜማው እንዲወገድ ፈልገው አይሁዶች:

«...ሥጋቸው በሰንበት በመስቀል ላይ እንዳይኖር፥ ጭናቸውን ሰብረው እንዲያወርዱአቸው ጲላጦስን ለመኑት። ጭፍሮችም መጥተው የፊተኛውን ጭን ከእርሱም ጋር የተሰቀለውን የሌላውን ጭን ሰበሩ፤ ወደ ኢየሱስ በመጡ ጊዜ ግን እርሱ ፈጽሞ እንደ ሞተ አይተው ጭኑን አልሰበሩም፤... »(ዮሐንስ 19:31-33)።

ቀደም ሲል ከጠቀስናቸው ክፍሎችና በኢንጅል ከሠፈሩ ሌሎችም የምንረዳው፥ መሢሑ ኢየሱስ ሲሰቀል የነበረው ገዥ ጲላጦስ እንደ ነበርና ይህም እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ከ26-36 ዓመተ ምሕረት እንደሆነ ታሪክ ይመዘግባል። ስለዚህ ኢየሱስ የሞተበት ጊዜ፥ በዚሁ በጲላጦስ የሥልጣን ዓመታት ውስጥ እንደሆነ ማስተዋል ይቻላል።

የሚመጣውም አለቃ ሕዝብ ከተማይቱንና መቅደሱን ያጠፉሉ፤ ፍጻሜውም በጐርፍ ይሆናል፥ እስከ መጨረሻም ድረስ ጦርነት ይሆናል፤ ጥፋትም ተቀጥሮአል»።

## 4. የትንቢተ ዳንኤል አፈጻጸም

«...የሚመጣውም አለቃ ሕዝብ ከተማይቱንና መቅደሱን ያጠፉሉ...»

ዳንኤል የኢየሩሳሌምን የቤተ መቅደሱን መፈራረስ አስመልክቶ የተናገረው ትንቢት በእርግጠኝነት እንደሚፈጸም መሢሑ ኢየሱስም ራሱ ከስቅለቱ ከጥቂት ቀናት በፊት ተናግሯል። ኢየሱስ በተናገረው ላይ ብናተኩር:-

«ኢየሩሳሌም ግን በጭፍራ ተከባ ስታዩ በዚያን ጊዜ ጥፋትዋ እንደቀረበ እወቁ» (ሉቃስ 21:20)።

ኢንጅል ደግሞ እንዲህ ዘግቦአል፡-

> «አንዳንዶቹም ስለ መቅደስ በመልካም ድንጋይና በተሰጠው ሽልማት እንዳጌጠ ሲነጋገሩ፡- ይህማ የምታዩት ሁሉ፥ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ በዚህ የማይቀርበት ዘመን ይመጣል አለ» (ሉቃስ 21፡5-6)።

ይህ ትንቢት እንደ አውሮጳ አቆጣጠር በ 70 ዓመተ ምሕረት በሚሰቀጥጥ ሁኔታ ተፈጸመ። በጄኔራል ቲቶስ መሪነት በኢየሩሳሌም ላይ የተነሣው የሮማ ሠራዊት ከተማይቱንና መቅደሱን እንዳልነበሩ አደረገ። በዚሁም ትንቢቱ ሙሉ በሙሉ ተፈጸመ። ዮሲፈስ የተባለ አይሁዳዊ ታሪክ ጸሐፊ በጊዜው የተከሰቱትን ሁናቴዎች በጽሑፉ እንዲህ ጽፎአል፡- «ሰዎች የነበሩበት ቦታ ነው ለማለት አያስችልም። ጎብኚዎችን ለማሳመን የሚያስችል አንዳችም ቅሪት አልነበረም።»

ከተመለከትናቸው መጻሕፍት ሁሉ የመሢሑ ኢየሱስን ሞት በተመለከተ የምንማራቸው ይኖሩናል። እንደሚከተለውም መዘርዘር ይቻላል፡-

ሀ) በቶራኽ ውስጥ እንደተጻፈው፥ ትንቢተ ዳንኤል መሢሑ ከኢየሩሳሌምና ከመቅደሱ መፈራረስ በፊት እንደሚገደል ግልጥ አድርጎ አሳይቶናል።

ለ) ከብዙ መቶ ዓመታት በኋላም በኢንጅል ውስጥ እንደተጻፈው፥ መሢሑ ኢየሱስ የዳንኤልን ትንቢት አረጋግጦ ራሱን ለሞት አሳልፎ የሚሰጥበትን ምክንያትም ዘርዝሯል።

ሐ) በተጨማሪ ኢንጅል መሢሑ በመስቀል መሞቱን አትቶ የዘመኑ የይሁዳ ምድር ገዥ ጲላጦስ እንደ ነበርም መዝግቦታል። የዳንኤልና የመሢሑ ኢየሱስ ትንቢቶች በእግዚአብሔር ኃይል የተነገሩ በመሆናቸው የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሆን ዘንድ የመሢሑ ኢየሱስ መሞትና ከመቃብር መነሳት የተገባ ሆኖ ተፈጸመ።

እንደ ኢንጅሉ መሠረት፥ ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ ለሐዋርያቱ እንዲህ አላቸው፡- «ከእናንተ ጋር ሳለሁ በሙሴ ሕግና በነቢያት በመዝሙራትም ስለ እኔ የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ይገባል ብዬ የነገርኋችሁ ቃሌ ይህ ነው አላቸው። በዚያን ጊዜም መጻሕፍትን ያስተውሉ ዘንድ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው፤



እንዲህም አላቸው፡- ክርስቶስ መከራ ይቀበላል በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሣል፥ በስሙም ንስሐና የኃጢአት ስርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በአሕዛብ ሁሉ ይሰበካል» (ሉቃስ 24፡44-47)።

ውድ አንባቢ፥ ኢንጅል እንዲህ ሲል ያረጋግጥልሃል፡-

> «ኃጢአተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ የሚለው ቃል የታመነና ሁሉ እንዲቀበሉት የተገባ ነው፤» (1ኛ ጢሞቴዎስ 1፡15)።
>
> «ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይህ ነው። አንድ እግዚአብሔር አለና፥ በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፥ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ ራሱንም ለሁሉ ቤዛ ሰጠ፥» (1ኛ ጢሞ.2፡4-6)።
>
> «እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው» (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡21)።
>
> «ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለ ዓመፀኞች አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሞቶአልና፤ በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ» (1ኛ ጴጥሮስ 3፡18)።
>
> «በዚህ ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው፥ ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው፤ ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ፥ መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው» (ፊልጵስዩስ 2፡9-11)።

**ልብ በል ፡-** መሢሑ ኢየሱስን እንደ አዳኝህና ጌታህ ትቀበለው ዘንድ እግዚአብሔር ፈቃዱ ነው። ኢየሱስን እንደ አዳኝህ በተቀበልህ ጊዜ ለኃጢአትህ ሁሉ ይቅርታን ታገኛለህ። እግዚአብሔርም ሰማያዊ አባትህ እንደሆነ ትረዳለህ። መንግሥተ ሰማይም የምትገባበት ዋስትና ይኖርሃል። መሢሑ ኢየሱስን እንደ አዳኝህ ለመቀበል ቁርጠኛ ፍላጎት ካደረግህ የሚከተለውን ጸሎት መጸለይ ትችላለህ። እግዚአብሔርም ይሰማሃል።

ኃያሉ እግዚአብሔር ሆይ፥ መሢሑ ኢየሱስ እንደሚወለድ፥ ለሥቃይና ለሞትም እንደሚዳረግና የሚጎናጸፈውን ታላቅ ክብር ሁሉ በመግለጽ ወደ ዓለም ከመምጣቱ ከብዙ ዓመታት በፊት ጀምረው ነቢያት እንዲጽፉ ስላደረግህ አመሰግንሃለሁ። በመሢሑ ኢየሱስ በኩልም ለእኔ ያለህን ፍቅር ስለ ገለጽክልኝ በጣም አመሰግንሃለሁ። ለኃጢአቴ ስርየት መሢሑ ኢየሱስ ራሱን ለሞት አሳልፎ እንዲሰጥ ስላደረግክ አመሰግንሃለሁ። የዘለዓለምን ሕይወት እጎናጸፍ ዘንድ መሢሑ ኢየሱስን ከሞት ስላስነሣኸው አመሰግንሃለሁ። ኃጢአተኛ መሆኔን ጠንቅቄ አውቃለሁ። ኃጢአቴን ይቅር ትለኝ ዘንድም እለምንሃለሁ። ለእኔ ሲል ሕይወቱን ለሞት አሳልፎ በሰጠው በመሢሑ ኢየሱስ ምክንያት ያገኘሁትን የኃጢአት ስርየት በዚችው ደቂቃ እቀበላለሁ። መሢሑ ኢየሱስ ጌታዬ ይሆን ዘንድ ፍላጎቴ ነው። ኢየሱስ ለሁሉ ያለውን ፍቅር ያህል እኔም ሌሎችን እወድ ዘንድ የዘለዓለም እርዳታህ አይለየኝ። ከኃጢአቴ ስላነጻኸኝ አመሰግንሃለሁ። ስለተቀበልከኝም አመሰግንሃለሁ። ይህን ሁሉ ጌታዬና አዳኜ በሆነው በመሢሑ ኢየሱስ ስም እለምንሃለሁ! አሜን።